ብርሃን
Berhan Bank

**የማህበሩ ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ 3,357,946,000**

**የምዝገባ ቁጥር 06/1/28428/01**

# ለብርሃን ባንክ አ.ማ. ባለአክስዮኖች የተላለፈ የጉባኤ ጥሪ

የብርሃን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 14ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሐሙስ ኅዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2:00 ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ፤ ቦሌ በሚገኘው ሚሊኒየም አዳራሽ ይካሔዳል፡፡ ስለሆነም የባንኩ ባለአክሲዮኖች በሙሉ በተጠቀሰው ቀንና በታ ማንነታችሁን የሚገልጽ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪ ያቀርባል፡፡

**የጉባኤው አጀንዳዎች**

1. አጀንዳውን ማጽደቅ
2. የተከናወኑ የአክስዮን ዝውውሮችን ማጽደቅና አዳዲስ ባለአክስዮኖችን መቀበል
3. በተጓደሉ የቦርድ አባል ምትክ የተተኩትን ዳይሬክተር ሹመት ማጽደቅ
4. የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ. የ2022/23 ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ
5. የውጭ ኦዲተሮችን እ.ኤ.አ. የ2022/23 ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ማዳመጥ
6. ከዚህ በላይ በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ መወሰን
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴን ሪፖርት መስማትና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መምረጥ
8. እ.ኤ.አ. በ2022/23 በጀት ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ወርኃዊ አበልና ዓመታዊ ክፍያ መወሰን እና
10. የጉባዔውን ቃለጉባዔ ማጽደቅ

**ማሳሰቢያ**

በጉባኤው ላይ ለመገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች

- ጉባኤው ከሚካሄድበት ቀን አስቀድሞ ባሉት ቀናት ውስጥ የባንኩ ዋና መ/ቤት አድራሻ በሆነው በአዲስ አበባ ከተማ፤ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 2185 በሆነውና ቦሌ ድልድይ ፊት ለፊት በሚገኘው የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት የአክስዮን አስተዳደር ክፍል በመገኘት የውክልና ፎርም/ቅጽ በመሙላት ተወካይ በመወከል ወይም
- በስብሰባው ለመገኘትና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ማስረጃ ያለው ተወካይ ዋናውን እና አንድ ፎቶ ኮፒ በጉባኤው ዕለት ይዞ እንዲቀርብ በማድረግ በወኪሎቻቸው አማካይነት መሳተፍ ይችላሉ፡፡

**የብርሃን ባንክ አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**

Tel +251 116 18 57 22 / +251 116 18 57 32 / +251 116 63 20 83
Fax +251 11 662 3431 Swift BERHETAA
E-mail info@berhanbanksc.com www.berhanbanksc.com
P.O.Box 387 Code 1110, Addis Ababa,Ethiopia

Follow us